የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን
የዋሽንግተን ዲሲ እና አካባቢው
ሀገረ ስብከት ጽሕፈት ቤት

The Ethiopian Orthodox Tewahedo Church
Archdiocese of Washington DC
and its surroundings.

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

ነሐሴ 13 2004 ዓ. ም

# ሕያው ሆኖ የሚኖር፥ ሞትንስ የማያይ ማን ነው መዝ 89:48

<u>የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ዜና እረፍትን አስመልክቶ ከዋሽንግተን ዲሲና አካባቢው ሀገረ ስብከት የተሰጠ መግለጫ</u>

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን 5ኛ ፓትርያርክ የነበሩት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ባደረባቸው ሕመም ምክንያት ነሐሴ 10 ቀን 2004 ዓ. ም ከዚህ ዓለም በሞት መለየታቸውን በመስማታችን በዋሽንግተን ዲሲና አካባቢው ሀገረ ስብከት ሥር የምንገኝ አብያተ ክርስቲያናት፤ ካህናት፤ ምእመናን እና ሰንበት ት/ቤቶች ከፍተኛ ሀዘን ተሰምቶናል። ብፁዕ ወቅዱስ አባታችን ላለፉት 21 ዓመታት አባታዊ መመሪያ በመስጠት፤ በቀድሞ መንግሥት የተወረሱ ቤቶችንና ተቋማትን በማስመለስ፤ የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ እንዲከፈት በማድረግ፤ ዘመናዊ ትምህርት ቤቶች እና አብያተ ክርስቲያናት ቋሚ ገቢ የሚያገኙባቸው ተቋማት እንዲከፈቱ መመሪያ በመስጠት፤ በተለይም የቤተ ክርስቲያንን ዓለማቀፋዊ ግንኙነት በማጠናከር እና በኢትዮጵያ ውስጥ የጤና እና ማኅበራዊ ችግሮች እንዲቃለሉ በማድረግ ረገድ ባደረጉት አስተዋጽዖ በኢትዮጵያ ሕዝብ፤ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እና በዓለም አቀፉ ተቋማት በታሪክ ሲታወሱ ይኖራሉ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ከግብጽ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጋር የበለጠ በመቀራረብ በጋራ ጉዳዮች አብሮ ለመሥራት የሚረዱ የጋራ ስምምነቶች የተፈረሙት በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ዘመነ ፐትርክና ነው። በተለያዩ የሃይማኖት ተቋማት መካከል ተግባብቶ መሥራት እንዲጠናከር በአገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ደረጃ ባደረጉት አስተዋጽኦ አለማቀፋዊ ክብርና ሽልማት ተሰጥቷቸዋል። የዋሽንግተን ዲሲና አካባቢው ሀገረ ስብከትም የብፁዕ ወቅዱስ አባታችንን ነፍስ በገነት ያኑርልን ይላል።

የብፁዕ ወቅዱስ አባታችን ዜና እረፍት የተሰማው፤ ቤተ ክርስቲያን ዘርፈ ብዙ ችግሮች በከበባት ጊዜ በመሆኑ የእምነቱ ተከታዮች በሙሉ በንቃት ቤተ ክርስቲያንን ለመጠበቅ በመንፈሳዊ ንቃት መጠናከር እንዳለብን የሚያሳስብ ነው።

በዚህ የሽግግር ወቅት ቤተ ክርስቲያን የተመሰረተችበትን ዓላማ ተግባራዊ እንዳታደርግ እንቅፋት የሆኑ ምክንያቶች ተለይተው ዘላቂ መፍትሔ ለመስጠት ስለሚያስፈልግ ሁሉም የእምነቱ ተከታዮች የቅዱስ ሲኖዶስን መመሪያ በመከታተል፤ የድርሻችንን ለመወጣት መዘጋጀት ይገባናል ። ሀገረ ስብከታችንም የቤተ ክርስቲያን አንድነቷ መዋቅሯ እና ሥርዓቷ እንዲጠበቅ የሚያደርገውን እንቅስቃሴ የበለጠ በማጠናከር ከቅዱስ ሲኖዶስ ጽ/ቤትና ከመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት ጋር በቅርበት ይሠራል ።

በዋሽንግተን ዲሲና አካባቢው ሀገረ ስብከት ሥር የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ነሐሴ 11 ቀን 2004 ዓ. ም ባደረጉት አስቸኳይ ስብሰባ የብፁዕ ወቅዱስ አባታችን ፀሎተ ፍትሐት አብያተ ክርስቲያናት፤ ካህናት፤ ምእመናን፣ የሰንበት ት/ቤቶች አባላት፤ የማኅበራት ተወካዮች፤ የአኀት አብያተ ክርስቲያንና የዓለም አቀፍ ተቋማት ተወካዮች በተገኙበት ሐሙስ ነሐሴ 17 ቀን 2004 ዓ. ም ከጧቱ 12 ፡00 ሰዓት ---- ቀኑ 5 ሰዓት / **Thursday, August 23, 2013** ,6:00 AM-----11:00 AM / በመንበረ ጵጵስና ምሥራቀ ፀሐይ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን አሌክሳንድርያ እና በአትላንታ ደብረ ጽዮን ወአቡነ አረጋዊ ቤተ ክርስቲያን እንዲደረግ ወስኗል። በዚሁም መሰረት በተለያዩ የሀገረ ስብከቱ ክልል ውስጥ የምትገኙ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ተከታዮች በተጠቀሰው ቦታ በመገኘት በጸሎተ ፍትሐቱ ሥነ ሥርዓት እንድትካፈሉ ጥሪ እናስተላልፋለን።

የዋሽንግተን ዲሲና አካባቢው ሀገረ ስብከት ጽ/ቤት